# በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንናተግባር እንዲሁም አሰራር ለመወሰን የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ ቁጥር -----/2012

ሚያዝያ/2012 ዓ.ም

ሀዋሳ

# መግቢያ

የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ እና በሀገሪቱ እየተካሄደ ያለዉን ለዉጥ ዉጤታማ፣ ዘላቂና ተቋማዊ ለማድረግ እንዲሁም ዕድገቱን በላቀ ደረጃ ለማፋጠንና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በብቃት ለመወጣት ብሎም ክልሉ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንጻር የመንግስት የልማት ድርጅቶች በመንግስት ይዞታ ስር እስካሉ ድረስ ዉጤታማ፤ ምርታማና አትራፊ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች በማቋቋምያ ህጎቻቸው የበላይ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን እንዲሆን የተወሰነው የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እንዲሁም ለድርጅት ቦርድ ሲሆን ራሱን የቻለ ተቆጣጣሪ አስፈጻሚ የመንግስት አካል በማቋቋም የልማት ድርጅቹ ተጠሪነት ለዚሁ አካል እንዲሆን በማስፈለጉ፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የአሰራር ነጻነት የሚያገኙበትን እና ስርዓታቸውን ለማዘመን መዋቅርና ሥርዓት ለመዘርጋ፤ ከግል ኩባንያዎች ጋር እየተወዳደሩ ለመስራት የሚያስችላቸዉን የብቃት አቅጣጫ ለመቀየሥ፤ የተቋቋሙበትን ዓላማ ከግብ እንዲያደርሱ፤በተናጠል ክትትል እና ቁጥጥር ሥር ሆነው ከሚሰሩ ግልጽ ተልኮን የሚሰጥየመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 180/2012 አንቀጽ 34(6) መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፤

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በአዋጁ አንቀፅ 38(1) በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን ስልጣን እና ተግባር እና አሰራር ለመወሰን ይህን ድንብ አዉጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

1. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ “የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባርእና አሰራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር …./2012” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **<u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፣

1. **“መንግስት”** ማለት የደቡብ ብሔሮች ፤ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ነዉ፤
2. **“ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን”**ማለት በአዋጅ ቁጥር 180/2012 አንቀጽ 34(6) የተቋቋመው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው፤
3. **“የመንግሥት የልማት ድርጅቶች”** ማለት ለተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ተጠሪ እንዲሆኑ የተወሰኑ እና ወደፊት በውሳኔ ሊሆኑ የሚችሉየማምረት፤ የማከፋፈል፤ የመገንባት፤ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሌሎች የኢኮኖሚ ተግባራቶችንና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን በንግድ መልክ ለማካሄድ የተቋቋሙድርጅቶች ናቸዉ፤
4. **“ቦርድ”** ማለት የልማት ድርጅቶች በተቋቋሙበት ህግ መሰረት የተቋቋመ አመራርሰጪ አካል ነዉ፤
5. **“ጠቅላላ ንብረት”**ማለት የድርጅቶቹ ሚንቀሳቀስ እና ማይንቀሳቀስ ንብረቶች፤ ድርጅቶቹ ገና ያልተቀበሏቸዉ ገቢዎች ጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ሲሆን ግዙፍ ያልሆኑ ንብረቶችን፤ በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎችንና ሌሎች ገቢ መሆን ያለባቸዉ ሂሳቦችን ይጨምራል፤
6. **“የተጣራ ጠቅላላ ንብረት”**ማለት ከጠቅላላ ንብረት ላይ በተያዘዉ የበጀት ዓመት ዉስጥ የሚከፈሉ ዕዳዎች፤ በቅድሚያ የተከፈለ ገቢና ሌሎች ዕዳዎች ተቀንሰዉ የሚቀረዉ ንብረት ነዉ፤
7. **“ካፒታል”** ማለት አንድ ድርጅት በተቋቋመ ጊዜና ከዚያም በኋላ መንግስት የሚመድብለት የተጣራ ጠቅላላ ንብረት በተመደበበት ጊዜ ያለዉ ዋጋ ነዉ፤
8. **“የተጣራ ትርፍ”** ማለት ከገቢዎችና ከሌሎች ክፊያዎች ከተገኘዉ ገንዘብ ላይ ወጪዎችና በበጀት ዓመቱ ዉስጥ ለሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ በአግባቡ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች፤ የዕርጅና ቅናሽ /ዲፕሪሼሽን/፤ ወለድና ልዩ ልዩ ታክሶች ተቀንሰዉ የሚቀረዉ ሂሳብ ነዉ፤

9. **"የመንግስት የትርፍ ድርሻ"** ማለት ከተጣራዉ ትርፍ ላይ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች ገቢ የሚሆነዉ ገንዘብ ተቀንሶ የሚቀረዉ ሂሳብ ነዉ፤
10. **"ሰዉ"** ማለት ማንኛዉም የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ፤
11. በወንድ ፆታ የተገለፀዉ ድንጋጌ ለሴትም ያገለግላል፡፡

## 3.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

አግባብነት ባለው ህግ እንዲሁም ውሳኔ ለባለስልጣኑ ተጠሪ እንዲሆኑ በተደረጉ እና በሚደረጉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ ነው፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

## 4.<u>የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የተቋቋመበት ዓላማ፡-</u>

1. የመንግስት ልማት ድርጅቶች ውጤታማ፤ ተወዳዳሪና አትራፊ እንዲሆኑ የድርጅቱን አመራርና አስተዳደር መከታተል እንዲሁም ዘመናዊየኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋትና ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል፤
2. የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አስተዳደር የመንግስት የባለቤትነት የተቆጣጣሪ እና የአመራር ሰጪውን አካላት ኃላፊነትና ሚናን በለየ መልኩ መተግበሩን በማረጋገጥ የክልሉን መንግስት በልማት ድርጅቶች ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት ማስከበር፤
3. በመንግሥት የልማት ፖሊሲ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስምሪት መካከል የሚኖረውን ቅንጅት ማሳለጥ ናቸው፡፡

## 5.<u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በክልሉ መንግስት መቀመጫ ይሆናል፡፡

## 6.<u>የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ አደረጃጀት</u>

1. በክልሉ መንግስት የሚሾም ዋና ኃላፊ እናአንድ ምክትል ኃላፊ እንዲሁም፤
2. አስፈላጊየስራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## 7.የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

1. አግባብነት ካላቸው አካላት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ቦርድ አባላትንና ሰብሳቢን እንዲሁም የየተጓደሉ ቦርድ አባላት እና ሰብሳቢን ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር በመምከር ይሰይማል፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤ ዕቅዶቹን ያፀድቃል፤ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
3. የልማት ድርጀቶችን ሒሳብ የሚመረምር የውጪ ኦዲተር ይሰይማል፤ የውጪ ኦዲት ሪፖርቶችን ያፀድቃል፤ በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል፤
4. የመንግስት የልማት ድርጅቶች አፈፃፀም እና ተወዳዳሪነት እንዲሻሻል ለማድረግ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና ኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤
5. የልማት ድርጅቶችን መነሻ ካፒታል፤ የድርጅቶች ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ምክረ ሃሳብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. የመንግስት የልማት ድርጅቶች አስፈላጊ ችሎታ፤ ልምድ እና ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
7. በክልሉ መንግስት አጠቃላይ አመራርና አቅጣጫ በመምራት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል እንዲዛወሩ የአሠራር ሥርዓት የሚዘረጋበት አግባብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ እንዲሆንም ያደርጋል፤
8. አስፈላጊ ሲሆን በሥሩየሚገኙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንዲፈርሱ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሃዱ፤ እንዲሸጡ ወይም እንዲከፋፈሉ ለመስተዳድ ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል ያስፈፅማል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ሥርዓት ያዘጋጃል፤በቦርዱ በሚቀርብለት ሃሳብ መሠረት ከተጣራ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ ከልማት ድርጅቶች ለመንግስት ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ ክፍያ መጠንለመስተዳድር ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ሲወሰንምተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
10. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ መሰረዝን በሚመለከት ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
11. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን፤ የብድር አወሳሰድና አመላለሳቸውን በቅርበት ይከታተላል፤
12. የመንግስት የልማት ድርጅቱን የተፈቀደ ካፒታል በዚህ ደንብ አንቀፅ18(2) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ እንዲያልቅ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ የመጠባበቂያ ሂሳቦች

እንዲያዙ ወይም ከመንግስት ገንዘብ እንዲመደብ ለመስተዳድር ምክር ቤት ምክረ ሀሳብ ያቀርባል ሲወሰንምተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

13. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለምርምር እና ለፈጠራ በቂ በጀት እንዲመድቡ እንዲሁም የተገኘውን የምርምር እና የፈጠራ ውጤት የሚመለከተው አካል ለዚህ ተግባር ያስቀመጣቸውን አሰራር ተከትሎ እንዲያሰራጩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
14. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አፈፃፀም እና ሁኔታ የሚያሳዩ የመረጃ ሥርአት ያደራጃል፤ ማዕከላዊ አስቀማጭም ሆኖ ያገለግላል፣ የድርጅቶችን አፈፃፀም የሚመለከቱ የወል መረጃዎችን ያሳውቃል፤
15. ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ቦርድ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ስራ አስኪያጆች ቅጥር እና ስንብት ውሳኔ ከድርጅቶች ቦርድ ሲቀርብለት ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር በመምከር መርምሮ ያፀድቃል፤
16. የልማት ድርጅቶች ተሞክሮ የሚለዋወጡበትን መድረክ ያዘጋጃል፣ የድርጅቶቹን የአመራር አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
17. ከሕግ አግባብ ውጪ የተወሰዱ ንብረቶችን እና በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮችን በሥራ ላይ ባሉና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል፤
18. በመንግስት የልማት ድርጅቶ ውስጥ መንግስት ያለውን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤
19. የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት ያዘጋጃል፤ እንዲሁም የግምገማና የማበረታቻ አፈፃፀም አሠራር ሥርዓት ያዘጋጃል፤
20. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የመንግስት የልማት ፖሊሲወች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው አካል ጋር ይመክራል፤ ክትትልም ያደርጋል፤
21. የመንግስት ልማት ድርጅቶች በልዩ ሁኔታ ትርፋቸውን እንዲጠቀሙ ወይም ለማስፋፍያ እንዲያውሉ የሚያስችላቸውን የአሰራር ስርዐት ይዘረጋል፤
22. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ኪሳራ ሲያጋጥማቸው ምንጩን በጥናት በመለየት፤ አዋጭ የሆነ የወጪ ቅነሳ ሥርዓት አዘጋጅቶ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤
23. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የአጭር እና የረጅም ጊዜ ብድር ከባንክ የሚያገኙበትን የአሰራር ስርዓት አጥንቶ ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

24. የልማት ድርጅቶቹ የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት በተለይም ገንዘብና ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ያዘጋጃል ወይም ይዘረጋል፡፡ የልማት ድርጅቶቹን ውጤታማነት ይበልጥ ለማረጋገጥ የሚያስችል እና የሥራ ባህሪያቸውን ያገናዘበ ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ያወጣል፤

25. የባለስልጣኑን ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 8. የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ ዋና ኃላፊ ሥልጣን እና ተግባራት

1. የባለሥልጣኑን ሥራወች ይሰራል፤ያስተዳድራል፤

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. በዚህ ደንብ አንቀፅ 8 ሥር የተዘረዘሩትን የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራትሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. የባለሥልጣኑን የሰው ሃይል ፍላጎት በጥናት እና ሠራተኞች ቀጥር በመፈጽም በክልሉ በፐብሊክ ሰርቪስ ቢሮ ያስፀድቃል፤ ያስተዳደራል፤

ሐ. የባለሥልጣኑን ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ የሥራ እና የበጀት ዕቅድ ያዘጋጃል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ. ለባለስልጣኑ በተፈቀደለት የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሠ. ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች በሙሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ. የባለሥልጣኑን የአፈፃፀም ሪፖርት ለቢሮ ያቀርባል፤

ሰ. የባለሥልጣኑን የአደረጃጀት መዋቅር ያዘጋጃል፤

ሸ.ለሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለምክትል ኃላፊው እና ለሌሎች የባለሥልጣኑ ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

ቀ. ለባለስልጣኑ በህግ የተሰጡትን ስልጣን እና ተግባር ለመወጣት ተጨማሪ ተግባራትን ይፈፅማል ያስፈፅማል፤

## 9.የምክትል ኃላፊ ሥልጣን እና ተግባራት

1. ከዋና ኃላፊ በሚሰጠው የስራ መመርያ መሠረት የባለስልጣኑን ተግባርት በማቀድ፤ በማደራጀት፤ በመምራትና በማስተባበር ዋና ኃላፊውን ያግዛል፤
2. በዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤
3. ዋና ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፡፡

## 10.የተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድራቸው የልማት ድርጅቶች

ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ በክልሉ ምክር ቤት የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 180/2012 አንቀፅ 34(11) ላይ የተዘረዘሩትን የልማት ድርጅቶች ያስተዳድራል፤ይቆጣጠራል፡፡ ሆኖም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድራቸውን የልማት ድርጅቶችን ብዛት ሊጨምር ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

# የመስተዳድር ምክር ቤት ስልጣን እና ተግባር

## 11. የመስተዳድር ምክር ቤት ስልጣን እና ተግባር

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ደንብ በማውጣት ማቋቋም በህግ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. አንድ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንዲፈርስ፤ ከሌላ የመንግስት የልማት ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ፤እንዲከፋፈል እንዲሁም እንዲሸጥ ከባለስልጣኑ ምክረ ሀሳብ ሲቀርብለት ይወስናል፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅት መነሻ ካፒታል ይመድባል፤ካፒታል እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ፤መጠባበቅያ ሒሳብ እንዲያዝ ምክረ ሀሳብ ከባለስልጣኑ ሲቀርብለት ይወስናል፤
3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል የሚዛወሩበት የአሰራር ስርዐት በባለስልጣኑ ተጠንቶ ሲቀርብለት ይወሰናል፤
4. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የወጪ ቅነሳ ሥርዓት በባለስልጣኑ አዘጋጅቶ ሲያቀርብለት ይወስናል፡፡

# ክፍል አራት

## ስለ ድርጅቶች አወቃቀር፤ ስራ አመራር ቦርድ እና ካፒታል

### 12.የመንግስት የልማት ድርጅቶች አወቃቀር

ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. ዋና ሥራ አስኪያጅና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጆች፣
3. የልማት ድርጅቱ ዳይሬክቶሬቶች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

### 13. ስለ ስራ አመራር ቦርድ አመሰራረት፤ የአባላት ተዋጽኦና የአገልግሎት ዘመን

1.እያንዳንዱ ድርጅት ለባለስልጣኑ የሚኖረው ተጠሪነት እንደተጠበቀ ሆኖ ስራዎቹን በበላይነት የሚያስተባብርና በዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እየመከረ ውሳኔወችን የሚያሳልፍ የራሱ ስራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኃላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ አካል ይኖረዋል፤

2. የቦርድ አባላት ቁጥር ቢያንስ አምስት ሆኖ ከፍተኛው ደግሞ ከዘጠኝ ያልበለጠ ይሆናል፤

3. ሰብሳቢውን ጨምሮ የቦርድ አባላት ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር አስቀድሞ በሚደረግ ምክክር በባለሥልጣኑ ዋና ኃላፊው አማካኝነት ይሰየማሉ፤

4. በንዑስ ቁጥር 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርድ አባላቱ አሰያየም እና አመራረጥ በሙያ፤ በስራ ልምድና በግል ብቃት ላይ ተመስርቶ ይፈፀማል፤

5. የቦርድ አባል ተወዳዳሪ ያልሆነ የሌላ ድርጅት ቦርድ አባል ሆኖ እንዲያገለግል ሊሰየምና ተጨማሪ ተልዕኮ ሊሰጠው ይችላል፤

6. የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ከሶስት ዓመት የማያንስና ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ይሆናል፤ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ ሲታመንበት ማንኛውም የቦርድ አባል የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ ለዳግመኛ ጊዜ ሊሰየም ወይም ሊመረጥ ይችላል፤

7. የድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ የቦርድ አባላቱ የአገልግሎት ዘመን በአንድና ተመሳሳይ ጊዜ አያበቃም፤

8. ማንኛውም የቦርድ አባል አባልነቱን በገዛ ፈቃዱ የተወ እንደሆን ቦርዱ ተተኪ አባል እንዲተካ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፤

## 14.የቦርዱ ስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ሥርዓት

1. ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል፤ሆኖም አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት በዚህ ሳይወሰን ማካሄድ አይከለክልም፤

2. የቦርድ አባላት ስብሰባው ከመካሔዱ በፊት የመወያያ አጀንዳው በጽሁፍ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ያስፈልጋል፤

3. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የተገኙ እንደሆነ ምልዐተ-ጉባኤ ይሑናል፤

4. ማንኛውም ጉዳይ ለቦርድ ቀርቦ ከተመረመረ በኃላ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምጽ የተደገፈ እንደሆነ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ የሰብሳቢውን ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፤

5. ቦርዱ ከድርጅቱ ሰራተኞች መካከል ፀሀፊውን መርጦ ሊመድብ ይችላል፤

6. ፀሀፊው ቦርዱ የሚያካሂዳቸውን የእያንዳንዱን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ በሚገባ ይይዛል፤ በስብሰባው ላይ የተገኙት አባላትም በቃለ-ጉባኤው ላይ እንዲፈርሙ ይደረጋል፤

7. የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ በቦርድ ስብሰባዎች ላይ በአካል ሊገኝ እና ሊሳተፍ ይችላል፤ሆኖም ድምጽ የመስጠት መብት የለውም፤

8. በዚህ አንቀጽ ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌወች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ውስጣዊ የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዐት ደንብ ሊያወጣ እና በስራ ላይ ሊያውል ይችላል።

## 15.ስለ ቦርድ አባላት ሀላፊነት እና ተጠያቂነት

1. የቦርድ አባላት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጧቸውን ተግባራት በከፍተኛ ትጋትና በብርቱ ጥንቃቄ መፈፀም አለባቸው፤

2. አባላቱ ተግባራቸውን በአግባቡ ካለመፈፀማቸው የተነሳ በድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

## ክፍል አምስት

## የመንግስት የልማት ድርጅት ካፒታል

### 16. ድርጅት ለማቋቋም ስለሚያስፈልግ ካፒታል

1 ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ካፒታል ይኖረዋል፡፡

2 አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ለማቋቋም የሚያስፈልገውን መነሻ ካፒታል ተቆጣጣሪው ባለስልጣን ምክረ ሃሳብ ለመስተዳድር ምክር ቤት እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡ ካፒታሉ በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡ በዓይነት የተከፈለ ከሆነ ባለስልጣኑ በትክክል የተጣራ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡

### 17.ስለተከፈለና ስለተፈቀደ ካፒታል

1. ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ሲቋቋም ድርጅቱ የሚኖረው የተከፈለ ካፒታል መጠን ከተፈቀደው ካፒታል ሀያ አምስት በመቶ /25 በመቶ/ ሊያንስ አይችልም፤
2. የአንድ ድርጅት የተፈቀደ ካፒታል ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት አመት ውስጥ በሙሉ ተከፍሎ ማለቅ አለበት፤
3. የተፈቀደው ካፒታል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተወሰነው ጊዜ በሙሉ ተከፍሎ ካላለቀ ቢሮው የሶስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ የድርጅቱን ካፒታል ወደ ተከፈለው የካፒታል መጠን ዝቅ ያደርገዋል፡፡

### 18. የተከፈለ ካፒታል ስለመጨመር

የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ከድርጅቱ ገቢ ውስጥ ተቀናሽ እንዲሆን በማድረግ ወይም ለመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ በማስመደብ የድርጅቱን ካፒታል እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 19.ካፒታል ስለመቀነስ

የሶስተኛ ወገኖች መብት ሳይነካ የአንድ ድርጅት ካፒታል የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥም ሊቀንስ ይችላል፡-

1. የድርጅቱ ካፒታል እንዲቀንስ ኦዲተሮች ሀሳብ ሲያቀርቡ ፣
2. በድርጅቱ ቦርድ በሚቀርበው ሃሳብ መሠረት ካፒታሉ እንዲቀንስ ሲወሰን፣ወይም
3. የድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል በዚህ ደንብ አንቀጽ17 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ሲወሰን በሙሉ ተከፍሎ ያላለቀ ሲሆን፡፡

# ክፍል ስድስት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለ ድርጅቶች ሒሳብ እና ቁጥጥር ስርዐት

### 20.ስለ ሒሳብ አያያዝ መርሆች

ማንኛውም የልማት ድርጅት በንግድ አሰራር ተቀባይነት ያላቸውን የሒሳብ አያያዝና አጠባበቅ መርሆች በመከተል ሥራዎቹን ያከናውናል፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ባለስልጣኑ አስፈላጊ የሆኑ መመርያወች ሊያወጣ ይችላል።

### 21.ስለ ሒሳብ ዓመት፤ የሒሳብ አዘጋግና ስለ ዓመታዊ ዘገባዎች

1) የመንግስት ልማት ድርጅት የሒሳብ ዘመን በባለስልጣኑ የሚወሰን ይሆናል፤
2) የመንግስት የልማት ድርጅት ቢያንስ በሒሳብ ዓመቱ አንድ ጊዜ ሂሳቡን መዝጋት አለበት። ሒሳቡን የመዝጋቱ ተግባር የሂሳብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በዘጠና ቀን ጊዜ ውስጥ መፈፀም ይኖርበታል፤
3) የመንግስት ልማት ድርጅት ስላለፈው ዓመት የድርጅቱ ሠራተኞችና አቋሞች ሁኔታ፣ ስለተከናወኑ ተግባሮችና በቅርብ ሥራ ላይ ሊውሉ ስለታሰቡ ዋና ዋና ዕቅዶችና ኘሮግራሞች ጭምር ሪፖርት ያዘጋጃል፤
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት /2/ መሠረት የድርጅቱን ሂሳብ በወቅቱ አለመዝጋት በድርጅቱ ስራ ሀላፊወችን በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ይሆናል።

### 22.ስለመጠባበቂያ ሂሳቦች እና አጠቃቀማቸው

1. ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ ይመሰርታል፤ይይዛል፤
2. በሌላ ሕግ የተወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ከተጣራ ትርፍ ላይ አምስት/5/ በመቶ በየአመቱ እያነሳ ሕጋዊ መጠባበቂያው ሂሳብ የመንግስት ልማት ድርጅቱን ካፒታል ሃያ /20/ በመቶ እስኪያህል ድረስ ወደ መጠባበቂያ ሂሳቡ ያስገባል፤
3. ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ

   ሀ.በድርጅቱ ላይ የደረሱ ኪሳራዎችን ለመሸፈን ፣

   ለ.ያልታሰበ ወጪዎችንና ዕዳዎችን ለመሸፈን ሊውል ይችላል።

4. የማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ቦርድን እያስፈቀደ ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች እንዲያዙ ለማድረግና አጠቃቀማቸውንም ለመወሰን ይችላል፡፡

## 23.ስለ ግብር እና ቀረጥ ክፍያ

1. የግብር እና ቀረጥ ክፍያን በሚመለከት አግባብ ባላቸው ሕጐች የተደነገጉት በድርጅቱ ላይም ተፈጻሚወች ይሆናሉ፤
2. ድርጅቶች በሌላ ሕግ መሠረት ከግብር እና ቀረጥ ነጻ ለመሆን ያላቸውን መብትና ሌላም መብት ይህ ደንብ አያስቀርባቸውም፡፡

## 24.የመንግስት የትርፍ ድርሻ ክፍያ

በዚህ ደንብ አንቀጽ 7/9/ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የልማት ድርጅት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሰባት /7/ ወራት የመንግስትን የትርፍ ድርሻ ለመንግስት ፈሰስ ያደርጋል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ስለ ሒሳብ ምርመራና ቁጥጥር

## 25.ስለ ኦዲተሮች አሿሿም

1. በሌላ ሕግ ለክልሉ ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ሂሳብ ባለስልጣኑ በሚሰይማቸው የውጪ ኦዲተሮች ይመረመራል፤
2. ተቆጣጣሪው ባለስልጣን የሚሰይማቸው የውጪ ኦዲተሮች በክልሉ ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት የወጡ መመዘኛዎችን የሚያሟሉና ከማንኛውም አይነት ተጽዕኖ ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤
3. ተቆጣጣሪው ባለስልጣኑ የውጪ ኦዲተሮችን የሥራ ዘመን ይወስናል፡፡

## 26.ሂሳብ የማስመርመር ግዴታ

የተመርማሪውን የመንግስት የልማት ድርጅት ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጪ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም ለሂሳቡ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሳቡን የማስመርመርና አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## ድርጅቶች ስለሚዋሀዱበት፤ስለሚከፋፈሉበት እና ስለ መፍረስ

### 27.መርህ

1. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የመንግስት የልማትድርጅቶች አንዱ ሌላውን በመጠቅለልም ሆነ አንድ ሌላ አዲስ ድርጅት በመፍጠር በመስተዳድር ምክር ቤት ውሣኔ ሊዋሃዱ ይችላሉ፤
2. አንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አዲስ የልማት ድርጅቶች እንዲሆን በመስተዳድር ምክር ቤት ውሣኔ ሊከፋፈል ይችላል፤
3. የመዋሃዱም ሆነ የመከፋፈሉ ውሣኔ ተግባራዊ የሚሆነውን በዚህ ደንብ መሠረት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይሆናል፡፡

### 28. የወል ድንጋጌ

1) ከባለገንዘቦች ጋር የብድር ስምምነት ያደረገና ዕዳውን ገና ያልከፈለ የመንግስት የልማት ድርጅት በዚህ ደንብ መሰረት ከመዋሀዱ ወይም ወደ ሌሎች አዳዲስ ድርጅቶች ከመከፋፈሉ በፊት የአበዳሪውን እና የዋስትና ሰጪውን ስምምነት መጠየቅ ይኖርበታል፤

2) በዚህ ደንብ መሰረት እንዲዋሀድ ወይም ወደሌሎች አዳዲስ ድርጅቶች እንዲከፋፈል የታሰበ ማንኛውም ድርጅት አስቀድሞ ዕዳ ያለበት ሆኖ ሲገኝ በውህደቱ ወይም በክፍፍሉ ምክንያት እንደ አዲስ የሚፈጠረው ድርጅት በገንዘብ ጠያቂወች በኩል የሚፈለግበትን ዕዳ ለመክፈል የማይችል ስለመሆኑ የታወቀ እንደሆነ የመዋሀዱም ሆነ የመከፋፈሉ ውሳኔ አይሰጥም፤

3) የሚዋሀደው ወይም የሚከፋፈለው ድርጅት ካለፈው ግማሽ አመት መጀመርያ አንስቶ ውህደቱ ወይም ክፍፍሉ እስከተፈፀመበት ጊዜ ድረስ ያለው ሂሣብ በኦዲተር ይመረመራል፡፡

### 29.የመብትና ግዴታ መተላለፍ

1. በመዋሃድ ምክንያት ሕልውናውን የሚያጣ ድርጅት መብትና ግዴታ ወደሚጠቀልለው ወይም በመዋሃድ ወደ ሚፈጠረው አዲስ ድርጅት ይተላለፋል፡፡
2. የሚከፋፈል ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ አንቀጽ 30 የተመለከተው የመብትና ግዴታ ምደባ መሠረት በመከፋፈሉ ወደ ሚፈጠሩት አዲስ ድርጅቶች ይዛወራል፡፡

## 30.የሚከፋፈል ድርጅት መብትና ግዴታ

1. በመከፋፈል ላይ ያለ ድርጅት መብትና ግዴታ በመከፋፈል ወደ ሚፈጠሩት ድርጅቶች የሚመደበው በባለስልጣኑ ውሳኔ ይሆናል፡፡
2. ባለስልጣኑ የድርጅቱን መከፋፈል ውሣኔ የያዘና መብትና ግዴታው በመከፋፈሉ በተፈጠሩት ድርጅቶች መካከል እንዴት እንደተመደበ የሚያሳይ የተሟላ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡የሪፖርቱ አንድ ቅጂ በመከፋፈሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅት በሚቋቋምበት ጊዜ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
3. ባለስልጠኑ የሪፖርቱን ዋና ዋና ነጥቦች የያዘ መግለጫ በሰፊው በሚሰረጩ ጋዜጦች አማካኝነት በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋወች ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
4. በንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የሰፈሩት ድንጋጌወች ቢኖሩም በክፍፍሉ የተፈጠሩት ድርጅቶች ሁሉ የተከፈለው ድርጅት ለሶስተኛ ወገኖች የገባው ግዴታ በሚመለከት በአንድነት እና በነጠላ ሀላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

## 31.ስለድርጅቶች መፍረስ

ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡-

ሀ. በማቋቋሚያው ደንብ የተመለከተው የድርጅቱ የመቆያ ጊዜ ሲያልቅ ፣
ለ.የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበት ሥራ ሲያልቅ ፣
ሐ.የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበት ዓላማ ሲከሽፍ ወይም ሊፈፀም የማይችል ሲሆን ፣
መ. ከመቶ ሰባ አምስት /75 በመቶ/ የሚሆነው የተከፈለው የድርጅቱ ካፒታል ሲጠፋ፣
ሠ. የመስተዳድር ምክር ቤት የድርጅቱን ሕልውና የሚነካ ውሣኔ ሲሰጥ፣
ረ. የድርጅቱ መክሰር በውጪ ኦዲተሮች ሲረጋገጥ ወይም በፍርድ ቤት ሲወሰን ፣

## 32.በኪሣራ ጊዜ ስለሚደረግ የሂሳብ ማጣራት

1 የመክሰር ሥርዓትን በሚመለከት የንግድ ሕጉ በሚደነግገው መሠረት አስፈላጊው ለውጥ ተደርጎባቸው በመንግስት የልማት ድርጅቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2 በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው ቢኖርም ፍርድ ቤት የድርጅት መክሰር በንግድ ህግ መሠረት በአጭር ስነ-ስርዓት እንዲመራ ሊወስን ይችላል፡፡

## 33. ስለ ሂሳብ አጣሪወች አሿሿም፤ስላጣንና ተግባር

1) በዚህ ደንብ አንቀጽ 31 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተመለከቱት ሁኔታወች ሲያገጥሙ ባለስልጣኑ በክልሉ ዋና ኦዲተር መስርያ ቤት የወጡትን መመዘኛወች የሚያሟላ እና የድርጅቱን ሰራተኛ ያልሆነ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የሒሳብ አጣሪወችን ይሾማል፤ በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ደግሞ ሊሽር እና በምትካቸው ሌሎችን ሊሾም ይችላል፤

2) ሒሳብ አጣሪዎች በመፍረስ ላይ ያለውን ድርጅት መዛግብትና የሒሳብ ሰነዶች ይረከባሉ፤

3) ባለስልጣኑ በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ሒሳብ አጣሪወች በዚህ ደንብ መሰረት የድርጅቱን ንብረት በመረከብ ለቦርዱ እና ለዋና ሥራ አስኪያጁ የተሰጣቸውን ስልጣን እና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፡፡ሆኖም ሒሳብ አጣሪወቹ ያልተቋጩ ውሎች ከሚጠይቁት አፈጻጸም ወይም ለሒሳብ ማጣራቱ አስፈላጊ ሆነው ከተገኙት በስተቀር አዳዲስ የንግድ ስራወችን ሊጀምሩ አይችሉም፤

4) ቦርዱ ከባለፈው የሒሳብ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ የሒሳብ ማጣራት ተግባሩ እስከሚጀመርበት ቀን ያለውን ጊዜ የሚሸፍንና የድርጅቱን ጉዳዮች የሚመለከት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሒሳብ አጣሪወች እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤

5) ሒሳብ አጣሪወችና ቦርዱ የድርጅቱን መብቶችና ግዴታዎች ባጭሩ የያዘ መግለጫ በጋራ አዘጋጅተው ይፈራረሙበታል፤

6) ባለስልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ቦርዱና የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሂሳብ አጣሪዎቹን በስራቸው ያግዟቸዋል፡፡

## 34.ባለገንዘቦችን ስለመጥራት

1 ሒሳብ አጣሪወች ድርጅቱ የሚፈርስ መሆኑን በመግለጽ ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ በተገቢው የሰነድ ማስረጃ አስደግፈው ያቀርቡ ዘንድ ለባለገንዘቦች የማሳወቅ ሀላፊነት አለባቸው፤

2 ስማቸው በድርጅቱ መዝገብ ላይ ተይዞ ለሚገኘው፤ እንዲሁም በሌላ ሁኔታ ለታወቁ ባለገንዘቦች ጥሪው በደብዳቤ ይላክላቸዋል፤ሌሎች ባለገንዘቦችበሰፊው በሚሰራጭ የክልሉ ጋዜጣ በየሳምንቱ በሚወጡ ሶስት ተከታታይ ማስታወቅያወች ጠሪ ይደረጋል፤

3 ባለገንዘቦች ያላቸውን የገንዘብ ጥያቄ እንደነገሩ ሁኔታ ደብዳቤ ከደረሳቸው ወይም የመጨረሻው የጋዜጣ ማስታወቅያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ ጥያቄዎቻቸውን ማቅረብ አለባቸው፤

4 ሒሳብ አጣሪዎች ስለ ደርጅቱ የሒሳብ እንቅስቃሴ ተገቢውን መግለጫ አዘጋጅተው ስለዕዳው አከፋፈል ያላቸውን ሓሳብ፤ ስለ ባለገንዘቦች ዝርዝር እና የአከፋፈላቸው ቅደም ተከተል የሚኖር ከሆነም በመጨረሻ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፤

5 ባለስልጣኑ ሒሳብ አጣሪወች ያዘጋጁትን የሂሳብ እንቅስቃሴ መግለጫ መሰረት በማድረግና ለአከፋፈል ያቀረቡትን ሀሳብ በማመዛዘን፡-

ሀ) የገንዘብ ጥያቄያቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ላቀረቡ ባለገንዘቦች ክፍያው እንዲፈጸም ያዛል፤

ለ) የድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ ለባለገንዘቦች መከፈል ያለበትን ዕዳ የማይሸፍን ሆኖ ሲገኝ የሶስተኛ ወገኖችን መብት ሳይነካ እርሱ በሚያፀድቀው የሽያጭ ዘዴ የሒሳብ አጣሪዎች የድርጅቱን ንብረቶች እንዲሸጡ ሊፈቅድ ይችላል፤

6 ጠቅላላ ንብረት ዕዳውን ለመክፈል የማይችል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜና የተፈቀደው ካፒታል በሙሉ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ሒሳብ አጣሪወች ቀሪው ካፒታል እንዲከፈል ባለስልጣኑን ይጠይቃል፡፡

## 35.<u>የባለገንዘቦችን መብት ስለመጠበቅ</u>

1. የታወቁ ባለገንዘቦች በዚህ ደንብ አንቀጽ 35 ንዑስ ቁጥር 3 ስር በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ የገንዘብ ጥያቄያቸውን ሣያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ሊከፈላቸው የሚገባው ገንዘብ በባለ ገንዘቦቹ ስም በባንክ ተቀማጭ ይደረጋል፤

2. ባልተጠናቀቁ የድርጅቱ ስራዎች መነሻነት የሚቀርቡ የገንዘብ ጥያቄዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ እንዲሁም ባለገንዘቦቹ ዋስትና ያልተሰጣቸው ከሆነ ክርክር ያስነሱ እዳዎች ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ ክርክሩ እስከሚወሰንበት ቀን ድረስ ለብቻ ተቀማጭ ሆኖ ይያዛል፤

3. በዚህ ደንብ መሰረት የድርጅቱ ህልውና ካከተማ በኃላ የቀረበና በድርጅቱ መዝገብ ያልታወቀ ማናቸውም ዕዳ ባለገንዘቦቹ የገንዘብ ጥያቄያቸውን በተወሰነው ገዜ ውስጥ ሣይቀርቡ የቀሩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሆነ እንደሆነ በትርፍነት ለክልሉ መንግስት ከገባው ሀብት ላይ ተቀናሽ ሆኖ እንዲከፈላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም በሒሳብ አጣሪዎች ቸልተኝነት ምክንያት ዕዳው ያልተከፈላቸው ባለገንዘቦች ሒሳብ አጣሪወችን በሀላፊነት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## 36.የመጨረሻ የሀብትና ዕዳ መግለጫና የድርጅቱን መፍረስ ስለማስታወቅ

1 ባለገንዘቦች ገንዘቡ ከተከፈላቸው በኃላ ሊቀርቡ የሚችሉ የገንዘብ ጥያቄወችን ለመሸፈን የሚያስፈልገው ገንዘብ በዚህ ደንብ አንቀጽ 36 ንዑስ ቁጥር 2 ተቀማች ከሆነ በኃላ ሒሳብ አጣሪወች ድርጅቱ ትርፍ ሀብት ካለው ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ የሀብትና የዕዳ መግለጫ አዘጋጅተው ለባለስልጣኑ ያቀርባሉ፤ይህንኑ ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ እና ዋና ኦዲተር መስርያቤት በግልባጭ ያሳውቃሉ፤

2 የክልሉ ዋና ኦዲተር መስርያ ቤት አንዳች አስተያየት ቢኖረው ይህንኑ ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮና ለባለስልጣኑ ወድያውኑ ያሳውቃል፤

3. ባለስልጣኑ የክልሉን ዋና ፋይናንስ ቢሮ የቅድምያ ስምምነት ካገኛ በኃላ የመጨረሻውን የሀብት እና የዕዳ መግለጫ ሲያፀድቀው ወድያውኑ ድርጅት እንዲፈርስ መፈለጉን ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ያሳውቃል፤
4. መስተዳድ ምክር ቤትም ድርጅቱ የተቋቋመበትን ደንብ ይሰርዛል፤ከዚህ ጊዜ ጀምሮም የድርጅቱ ህልውና ያከትማል፤
5. የፈረሰው ድርጅት መዛግብት በባለስልጣኑ ዘንድ ተቀማጭ ሆነው ለ10 ዓመታት ይቆያል፤እነዚህን መዛግብት ለማየት የሚፈልጉ ሰዎችም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ማየትና መመርመር ይችላል፡፡

## 37.ለመንግስት ገቢ ስለሚሆኑ ሀብቶች

በዚህ ደንብ መሰረት የፈረሰና ሒሳቡ እንዲጣራ የተደረገ ማንኛውም ድርጅት ትርፍ ሀብት ቢኖር ለክልሉ መንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

# ክፍል ስምንት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 38.የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሂሳብ መዝገብ

1. የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል፡፡
2. የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ የሂሳብ መዝገብ እና ገንዘብን የሚመለከቱ ሠነዶች በየዓመቱ ለክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በሚመደቡ ኦዲተሮች ይመረመራል፡፡

## 39.<u>በጀት</u>

የባለ ስልጣኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

## 40.<u>በሌሎች ሕጐች ስለተቋቋሙ ድርጅቶች</u>

1. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ክልሉ ቀደም ሲል ባወጣቸው ሌሎች ሕግጋትና ደንቦች የተቋቋሙ ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ፣
2. ከዚህ ደንብ በኂላ በሚወጡ ደንቦች የመንግስት የልማት ድርጅቶችን እንደገና እንዲቋቋሙ ተከፋፍለው አዲስ በሚቋቋሙ ድርጅቶች እንዲተኩ ወይም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር እንዲዋሃዱ ወይም፣
3. በዚህ ደንብ መሠረት እንደተቋቋሙ ተቆጥረው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት እንዲተዳደሩ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 41.<u>ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጐች</u>

1. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. ደንብ ቁጥር 147/2008 አንቀጽ 9፤አንቀጽ10 (ንዑስ አንቀጽ 2፤3 እና 4) ፤አንቀጽ 11(ንዑስ አንቀጽ 8፤9፤10፤12፤13) ፤

ለ. ደንብ ቁጥር 80/2003 አንቀጽ 9 (ንዑስ አንቀጽ 1፤3፤4) ፤

ሐ. ደንብ ቁጥር 89/2003 አንቀጽ 7(ንዑስ አንቀጽ 1፤2፤3፤4) በዚህ ደንብ ተሸረዋል፡፡

## 42.<u>ስለሌሎች ህጎች ተፈፃሚነት</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በሌላ አኳሃን ካልተወሰነ በስተቀር ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱ የፍትሐብሔርና የንግድ ህጎች ድንጋጌዎች ባለስልጣኑ በሚያስተዳድራቸው የልማት ድርጅቶች ላይም በተመሣሣይ ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡

**43.** ***<u>መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን</u>***

ባለስልጣኑ ይህ ደንብ ለማስፈፀም የሚረዱትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**44.** ***<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>***

ይህ ደንብ ከመጋቢት ------- 2012 ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ሀዋሣ መጋቢት ---------- ቀን 2012 ዓ/ም*

**እርስቱ ይርዳው**

**የደቡብ ብሄሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት**

**ምክትል ርዕሰ መስተዳድር**